## ዩ ኤስ የሌበር ዲፓርትመንት
## **2018 የአስከፊ  የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ግኝቶች**

ኢትዮጵያ

እጅግ አስከፊ የሆኑትን የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛዎችን ለማስወገድ በ2018 ኢትዮጵያ መለስተኛ አዎንታዊ የሆነ እርምጃ አስመዝግባለች። ብሄራዊ ጸረ ሕገወጥ ዝውውር እና በድብቅ ስደተኞችን የሚያዘዋውሩትን ለመቋቋም የተሰማራው ግብረ ሃይል ከ አይ.ኤል.ኦ ጋር በመሆን የስደተኞችን ጉዳይ በሚመለከት ቅንጅትን እና ትብብርን ለማሻሻል ግልጋሎት ሰጪዎችን ለይቶ አመልክቷል፤ በተጨማሪም መንግስት የሠራተኞች ተቆጣጣሪዎችን ባጀት ከ 2017 ጋር ሲነጻጸር አራት እጥፍ ያህል አሳድጓል፤ ከአለም ባንክ እና ከ ዩ.ኒ.ሴፍ ጋር በመተባበር 117 ሚሊዮን መጽሃፍትን አከፋፍሏል፤ እንዲሁም የ260 አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ክፍሎችን ገንብቷል። ቢሆንም ግን፤ ሕጻናት ኢትዮጵያ ውስጥ አስከፊ በሆኑ ሥራዎች ላይ መሰማራታቸውን ቀጥለዋል፣ ተገደው የቤት ሠራተኛ በመሆን ጭምር፤ ደግሞም ሕጻናት አደገኛ በሆኑ የእርሻ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጉ ነጻ መሰረታዊ ትምህርትን አያካትትም ወይም ለትምህርት አነስተኛ የትምህርት ዕድሜ ላይ ያሉ በትምህርት ላይ መሰማራት አለባቸው ብሎ አያዝም፤ ይህም ሕጻናትን አስከፊ ለሆኑ ሥራዎች እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል። የሕጻናትን ሥራ የሚጻረሩ ማህበራዊ ፕሮግራሞች ከፍተኛ የሕጻናት ሥራ ባሉባቸው መስኮች ላይ በብቃት ያነጣጠሩ አይደሉም፡፡

በሪፖርቱ መሠረት አስከፊ የሚባሉትን የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛን ከኢትዮጵያ ለማስቀረት በይበልጥ ያግዛሉ የተባሉ የእርምጃ ምከረ ሃሳቦች ተለይተዋል፡፡

| **መስክ** | **የእርምጃ ምከረ ሃሳብ** | **የተፈጻሚነት ዓመት (ታት)** |
|---|---|---|
| የሕግ ማዕቀፍ | ከውል ውጪ የሚሠሩትን አካትቶ ሁሉም ሕጻናት፣ የሕጻን ሠራተኛ ሕግጋት ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 2009 – 2018 |
| | ለሕጻናት የተከለከሉ አደገኛ ሥራዎች ሽመናን ጨምሮ የልማድ ሥራዎች ሁሉን አካታች  መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡ | 2016 – 2018 |
| | ነጻ መሠረታዊ ትምሕርትን እና ከአነስተኛ የቅጥር ዕድሜ ጋር የተጣጣመ ትምሕርት አስገዳጅ የሚሆንበትን የትምሕርት ዕድሜ በሕግ መወሰን፡፡ | 2012 – 2018 |
| አፈጻጸም | የሥራ ሁኔታ መርማሪዎችን ለማጠናከር ቅጣት እንዲበይኑ ፈቃድ መስጠት፡፡ | 2013 – 2018 |
| | የሥራ ቦታ ደህንነት መርማሪዎች በሁሉም የሥራ ዘርፎች በሥርዓት የሚመራ ምርመራ ለማካሄድ በቂ ስልጠና እና ግብዓት ያላቸው መሆኑን እና ከሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር በብቃት መተባበር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ | 2009 – 2018 |
| | ቅጣቶች ከፍ ተደርገው ጥሰቶችን በማገድ አገር በቀልም ሆነ ኬላ ተሻጋሪ ሕገወጥ ሰዎች አዘዋዋሪዎች ላይ ምርመራ መካሄዱን ማረጋገጥ፡፡ | 2013 – 2018 |
| | አስከፊ ከሚባል የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛ ጋር በተያያዘ በተካሄዱ የወንጀል ምርመራዎች፣ በተገኙ የሕግ ጥሰቶች፣ በተጀመሩ የክስ ሂደቶች፣ በወንጀል ጥፋተኛ የመባል ውሳኔዎች ላይ መረጃዎችን ማሰባሰብ መከፋፈል እና ማሳተም፡፡ | 2009 – 2018 |
| | የሥራ ሁኔታ  መርማሪዎችን ቁጥር ጎላ ባለ መልኩ በመጨመር ከ(ILO) የቴክኒካል ምክር ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ማድረግ፡፡ | 2015 – 2018 |
| ማስተባበር | ሕገ-ወጥ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለመዋጋት ተግባራዊ የተደረጉ የማስተባበር ዘዴዎች ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ በቂ ገንዘብ የተመደበላቸው መሆኑን እና በብቃት ኮሚቴዎቹ መቀናጀት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ | 2015 – 2018 |

| መስክ | የእርምጃ ምክረ ሃሳብ | የተፈጻሚነት ዓመት (ታት) |
|---|---|---|
| የመንግሥት ፖሊሲዎች | በትምሕርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም፤ በብሔራዊ የቴክኒክ እና ሙያ ትምሕርት እና ሥልጠና ስትራቴጂ እና በብሄራዊ የወጣቶች ፓሊሲ ውስጥ የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛን ማስወገድ እና መከላከል ስትራቴጂዎችን ማዋሃድ፡፡ | 2013 – 2018 |
| | ያሉ ፓሊሲዎች እንደታቀዱት መተግረባቸውን ማረጋገጥ፡፡ | 2018 |
| ማሕበራዊ ፕሮግራሞች | በገጠራማ አካባቢዎች የትምሕርት ቤቶችን በማሳደግ፣ የትምህርት ቤቶቹን ርቀት በመቀነስ፤ ተጨማሪ መምህራንን በመቅጠር፤ የመጸዳጃ ተቐማትን በመገንባት፤ የትምህርት ቤት ወጪዎችን በማስወገድ፤ ሴት ልጆች ላይ የሚደርሰውን የጾታ በደልን እና ማስፈራራትን በመጋፈጥ፤ ትምህርት የማግኘት እድላቸውን ከፍ ማድረግ፡፡ | 2010 – 2018 |
| | ልጆችን በግብርና ወይም በቤት ውስጥ ሥራዎች ላይ ከመሰማራት ለመከላከል ወይም ከማንኛቸውም የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንዲርቁ ለማድረግ የማሕበራዊ ፕሮግራሞች ግሊጋሎቶችን በመተግበር እንደ ማቋቋሚያ እና መልሶ መወሃጃ ማእከላት የመሳሰሉትን በአገር ዙሪያ መኖራቸውን ማረጋገጥ፡፡ | 2009 – 2018 |